## I. የውጭ ጉዳይ ፕሮግራም

### 1. የኢህአዴግ ስትራተጅያዊ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አላማ

የኢህአዴግ ስትራተጅያዊ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አላማ የብሔራዊ ጥቅማችን እምብርት ለሆነውና ለምንገነባው የዴሞክራሲ ስርዓት፣ ለመንፈጥረው የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ የተመቻቸ አለማዊና ከባቢያዊ ሁኔታን መፍጠር፣ የብሔራዊ ጥቅማችንና ሉዐላዊነታችን ዋነኛ መገለጫ የሆኑትን እነዚህን ግቦች ማሳካት ይቻል ዘንድ ሰላም የሚሰፍንበትን ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡ ይህንን ስትራተጅያዊ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አላማ ለማሳካትም የሚከተለውን የውጭ ጉዳይ ፕሮግራም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### 2. የህዝቡን መብት ጥቅም የሚያስጠብቅ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን መከተል፣

17.1 የብሔራዊ ጥቅማችን መሰረትና ማዕከል ዴሞክራሲ በአገራችን ስር እንዲሰድ ፈጣን፣ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችንን የሚያጎለብት ልማት ማረጋገጥ መሆኑን በመገንዘብ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን በዚሁ የተቃኘና ይህንኑ የሚያገለግል እንዲሆን ማድረግ፣

17.2 ለዚሁ አላማ በሁሉም አገሮች ጋር የመልካም ወዳጅነት ትብብር ግንኙነት መመስረት ይህም የጋራ ጥቅምን በሚያስከብር አኳኋን እንዲቃኝ ማድረግ፡፡ የጋራ ጥቅምን የሚያራምዱ ተግባሮችን በሙሉ መደገፍ፣ የአገራችንን ጥቅም የሚፃረሩ ተግባሮችን በጥብቅ መቃወም፣ ማስወገድ፣

17.3 ከጎረቤት አገሮች ጋር ጠንካራ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስር በመፍጠር፣ የህዝቦችን ህብረትና ወንድማማችነት ማጠናከር፣

17.4 የአካባቢያችን ሰላም ለዴሞክራሲ ስርዓታችን ማበብና ለፈጣን እድገታችን ያለውን ከፍተኛ ጠቃሜታ በመገንዘብ አገራችን የአካባቢው ሰላም እንዲረጋገጥ ልታደርግ የምትችለውን የላቀ አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት ለአካባቢያችን ሰላምና መረጋጋት በፅናት መቆም፡፡ የአገሮችና ህዝቦች እኩልነት የጋራ ጥቅም በጋራ ማራመድን በውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ያለመግባትን መርህ የተከተለ ፖሊሲ መከተል፡፡ የአካባቢ ሰላም የሚያውኩ ሃይሎች ከዚሁ ተግባር እንዲቆጠቡ የተቀናጀ ፖለቲካዊ ዴፕሊማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ፡፡ይህንኑ ለሰላም፣ ከቆሙ ሃይሎች ጋር

በቅንጅት መፈፀም፡፡ በአገራችን ላይ የሚቃጣ ማንኛውንም የአመጽ ተግባር ለማስወገድ አበክሮ መንቀሳቀስ፣

17.5 ለአፍሪካ አንድነት በአፍሪካ ደረጃ ለሚካሄድ ትብብር በፅናት መቆም፡፡ አገራችን በአፍሪካ መድረኮች እያደገ የሚሄድ ገንቢ ሚና እንድትጫወት ማድረግ፣

17.6 ለሰላም፣ ለፍትህና ለማህበራዊ እድገት የሚደረጉ የአለም ህዝብ ጥረቶችን መደገፍ፣

## 3. የውጭ ጉዳይ ፕሮግራም የማስፈፀም አቅምን ማጎልበት፣

3.1 መንግስት የውጭ ጉዳይ ፕሮግራምን ለማስፈፀም፣ የአገራችን ብሔራዊ ጥቅምና ሉዐላዊነትን ለማስከበር የሚያስችል ብቃት ያለው አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖረው ማድረግ፡፡ በዘርፉ የሚካሄድ የሰው ሃይል ስልጠናን ማጠናከር፡፡ የአቅም ግንባታ ስራው በቀጣይነት እየተሻሻለና እየተጠናከረ እንዲሄድ ማድረግ፣

3.2 በውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ጉዳዮች ላይ ቀጣይ ምርምርና ጥናት የሚያካሂዱ፣ የምርምር ጥናት ተቋሞች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ማድረግ፡፡ የነዚህ ተቋሞ የምርምርና የጥናት ውጤት በውጭ ጉዳይ እንቅስቃሲያችን ላይ በቂ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ማድረግ፡፡

3.3 የውጭ ጉዳይ ፕሮግራም አስፈፃሚው አካል ፕሮግራሙን ለመፈፀም የሚያስችል ጠንካራ አመለካከትና እምነት እንዲሁም ሙያዊ ብቃት እንዲኖረው ማድረግ፣

## 4. ህዝቡ የውጭ ጉዳይ ፕሮግራም በማስፈፀም ስራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ማድረግ፣

4.1 ህዝቡ በመንግስት የውጭ ጉዳይ ፕሮግራም አፈፃጸም ላይ በቂ ተሳትፎ እንዲኖረው ለማድረግ መሰረታዊ አቅጣጫዎቻችንን እንዲጨብጥ በዚህ ጉዳይ ላይ ወቅታዊና በቂ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ፣

4.2 በወቅታዊ የውጭ ጉዳይ ፕሮግራም ነጥቦች ላይ ህዝቡና ሙያተኞች የሚወያዩባቸው የሚከራከሩባቸው መድረኮች እንዲኖሩ ማድረግ፡፡ መንግስት ከተለያዩ አገሮች ጋር የሚያደርጋቸው ውሎች፣ ግንኙነቶች አላማቸውና ይዞታቸው በአግባቡ እንዲታወቅና ውይይት እንዲደረግበት ማድረግ፣

4.3 በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአለም አቀፍ ህጎች መሰረት መብትና ጥቅማቸው እንዲከበር መታገል በአገሪቱ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የውጭ ጉዳይ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሰፊና ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ማበረታታት፣